የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

መግለጫ

No 3/8/2010
ቀን ሚያዝያ ፳፫ ፳፻፲ ዓ.ም
Date

# በስደት ላይ ከሚገኘውና ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የወጣ መግለጫ

በብፅዑ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፴፱ኛውን ስብሰባ በኒዮርክ ድብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካቴድራል ከሚያዝያ ፳ እስከ ፳፫ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም አካሄዷል።

ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ ተልኮ መፋጠንና ሰላም ስለ ሀገር አንድነትና ፍቅር ስለ ቀኖና ቤተክርስቲያን መጠበቅና ስለ ስብከተ ወንጌል ምስፋፋት ተወያይቷል። ጉባኤው በብፅዑ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎትና ቡራኬ ተጀምሯል። ከዚያ በኋላ በካቴድራሉ አስተዳዳሪ መላከ ገነት ገዛህኝ ገብረ ክርስቶስ እና የሰበካው ጉባዔው ጸሐፊ አቶ ግርማ ሞገስ የእንኳን ደህና መጣችው ንግግር አድርገዋል። ከዚያ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶስ በተዘጋጅው አጅንዳ መሰረት ደረጃ በደረጃ ጉባኤውን አካሄዷል። በስብሰባው ጊዜ በቅርቡ ስላረፉት ስለ ታላቁ ኦርቶዶክሳዊ አባት አቡነ ዜና ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ ዕረፍትና በስማቸው ስለሚደራጀው የሐመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ገዳም፣ እንዲሁም አጽማቸው በገዳሙ ከማረፉ አስቀድሞ ስለሚደረገው ቅድመ ዝግጅት በሰፊው ተወያይቷል። ብፁዕነታቸውንም በማሰብ ቅዱስ ሲኖዶስ ጸሎት አድርጓል። በብፁዕነታቸው ዕረፍት ጊዜ ሁለንተናዊ ድጋፍ ላደረጉት ግለሰቦች እና ልዩ ልዩ ተቋማት ቅዱስ ሲኖዶስ ምስጋና አቅርቧል። ከዚያም በኋላ ከልዩ ልዩ የመምሪያ ሀላፊዎች የሥራ ሪፖርት ቀርቦለታል። በ1999 ዓ.ም ለተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት በሊቀ ጵጵስና ማዕረግ እንዲያገለግሉ በማዕረግ ያሳድግ ሲሆን በአሜሪካ በአውሮፓ በአፍሪካ በአውስትራሊያ እየተዘዋወሩ ቤተክርስቲያንን የሚያስፋፉ አዲስ ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ከወዲሁ ጥናት እንዲጀመር ተስማምቷል። በብፁዕ አቡነ ኤልያስና በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በአፍሪካና በአውሮፓ የተካይሄደው ሐዋርያዊ ተልዕኮ እንቅስቃሴ ለጉባኤው ቀርቦ ሁልተናዊ ድጋፍ አግኝቷል። እንዲሁም የዜና ተዋህዶን የሬድዮ ቅድመ ገጽ አገልግሎት አስመልክቶ ሰፊ ውይይት አድረጓል። በራሳቸው አነሳሽነት ለቤተክርስቲያን አንድነትና ሰላም ሥራ የጀመሩትን «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት ጉባኤ» ልዑካን ተቀብሎ አነጋግሯል። ይዘው የመጡትንም ደብዳቤ በቅዱስ ሲኖዶስ ፊት እንዲነበብ ከአደረገ በኋላ ለቤተክርስቲያን አንድነትና ሰላም ቅዱስ ሲኖዶስ ሁል ጊዜ የሚሠራ የሚሆኑን ገልጦ የልዑካኑን መልክት ተቀብሎ ልዑካኑን አሰናብቷል። በጠቅላላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሰላም፣ ስለ ሀጋራችንና ሕዝባችን ውቅታዊ ሁኔታዎች በሰፊው ከተነጋገረ በኋላ ለቤተክርስቲያንና ለሀገር የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን በማስተላላፍ ከዚህ የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

1. በሰሜን አሜሪካ የመጀመሪያው የሆነውን የሐመረ ኖህ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያን የአቡነ ዜና ማርቆስ መታሰቢያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ገዳም ግንባታና አድረጃጀት ተግባር በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል፣



4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

የብፁዕነታቸው አጽም በገዳሙ ውስጥ እንዲያርፍ የሚደረገው ቅድመ ዝግጅት በፍጥነት እንዲጠናቀቅ ውስኗል። ለገዳሙ በመላው አሜሪካ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት እና ምዕመናን የሚያደርጉትን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ቅዱስ ሲኖዶስ ያደንቃል።

2. በ1999 ዓ.ም በጥር ወር የተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳትን ከዛሬ ጀምሮ በሊቀ ጵጵስና ማዕረግ እንዲያገለግሉ ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነ ሲሆን በአሜሪካ በአውሮጳ በአውስትራልያ እና በአፍሪካ በምስፋፋት ላይ የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እድገት ለማፋጠን ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ ጥናት ይደረግ ዘንድ ወስኗል።

3. በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት እና በአባ ውልደ ትንሳኤ አያልነህ በአውስትራልያና በአፍሪካ በመካሄድ ላይ ያለው የስብከተ ውንጌል ሐዋሪያዊ ጉዞ እንዲቀጥል ወስኗል። ሌሎች መምህራንም በሐዋሪያዊ ጉዞው እንዲሳተፉ መመሪያ ሰጥቷል።

4. ዜና ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሬድዮና ቅድመ ገጽ አግልግሎት ተጠናቅሮ እንዲቀጥል፣ በሳተላይት ወደ ኢትዮጵያ የሚተላላፈውን የቴሌቭዥን አግልግሎት አጥንቶ ወደ ኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ሐዋርያዊ መልክት እንዲተላለፍ አጥንቶ እንዲያቀርብ መመሪያ ለዝግጅት ክፍሉ አስተላልፏል።

5. ቅዱስ ሲኖዶስ በስደት የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አገልግሎት በብቃት ለማከናውን ዘመኑን እና የዘመኑን ሂደት የተገነዘቡ፣ ጊዜውን የሚዋጅ ሐዋርያዊ ተዕልኮ የሚያበረከቱ፣ የሕዝባችንን ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ሕይዎት በሚገባ የተረዱ ካህናት እንደሚያስፈልጉ ያምናል። ስለዚህ በሰሜን አሜሪካ የምትገኘውን ቤተክርስቲያን ለሚያገለግሉ ካህናት ውቅታዊ እና ትምህርታዊ ሴሚናር እንዲዘጋጅ ቅዱስ ሲኖዶስ የወሰነ ሲሆን ይህንን ውሳኔ ወደ ተግባር የሚለውጡ ኮሚቴዎችን አዋቅሯል። ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ ሁሉም ማኅበረ ካህናት እና አብያተ ክርስቲያናት እንዲተባበሩ ጥሪ አቅርቧል።

6. ለሀገርና ለቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት ቅዱስ ሲኖዶስ በትጋት የጸልያል። ለሰላምና አንድነት ከሚሠሩ ጋር አጋርነቱን ሁል ጊዜ በቃልም በጽሑፍም ሲገልጥ ቆይቷል። አሁንም በራሳቸው አነሳሽነት «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት ጉባኤ» በሚል ተሰባሰበው ስለ ቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት የሚሠሩትን ጉባኤ አባላት አራት ልዑካን ካህናት ተቀብሎ አነጋግሯል። ለሰላምም ሁል ጊዜ የሲኖዶስ በር የተከፈተ እንደሆነ ለሁሉም ገልጧል። በቀኖና መጣስ ምክንያት በስደት ላይ የሚገኙት ሕጋዊው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሰለቤተክርስቲያን ህግ መጠበቅ ሁልንተናዊ ዋጋ በመክፈል ቤተክርስቲያንንም በዓልም ዙሪያ በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ። ስለ ዚህ ለቤተክርስቲያን ሰላምና አንድነት የሚደረገውን ጥረት ሁሉ ይደግፋሉ።

7. አንድ ሀገር ሊበልጽግና ሊያድግ የሚችለው የተረጋጋ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቅም ሲኖረው ነው። ሀገራችን ባልንበት ዘመን አስከፊ ገጽታ ከሚታይባቸው አንዷና የመጨረሻም ሆና መታየቷን አሁን ያለው መንግሥትና በተቃዋሚ ጎራ ያሉ ወገኖች አርቆ ሊያስቡበት ይገባል ብሎ ቅዱስ ሲኖድስ ያምናል። በመሆኑም በቅርቡ በሀገራችን በሚደረገው ሀገራዊ ምርጫ በስላጣን ላይ ያለው አካልም ሆነ ተቀዋሚዎች እንደ አለፈው ጊዜ ለብዙዎች ኢትዮጵያውያን መከራን የማያስከትል ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ቅዱስ ሲኖድስ ጥሪውን ያስተላልፋል።

አምላካችን እግዚአብሔር ቅድስት ቤተክርስቲያንንና ሀገራችንን ይባርክ።

Aba Yoseph Bishop of Nevada,
Arizona, Idaho & the exiled
E.O.T.C Holy Synod vice secretary